# ለምን ይሆን?

ታሪክ ይዘን የሚያኮራ፣
ትውልድ ይዘን የሚሰራ፣
ከምሁር እስከ ደብተራ፣
ታዲያ ምነው የኛ ተራ፣
ሁል ጊዜ ሆነ ውራ።

አፈር ጠፉ የሚታረስ፣
ቀላይ ምንጩ ሰርክ የሚፈስ፣
ምድሩ ሰጪ ፍሬ ለጋሽ፣
አዝእርቱ ህይወት አዳሽ፣
ሆኖ እያለ ሁሉ ሙሉ፣
የኛ ተራ ድልድሉ፣
ከበስተኋላ መዋሉ፣
ለምን ይሆን ዛሬም ድረስ፣
የችጋር ጠኔ ኣጋሰስ
የሚኖር ሲመላለስ።

ለምን?

አለም ዘምኖ ሲመጥቅ፣
እኛ ግን በታሪክ ትጥቅ፣
በተረት ተረት ስንቅ፣
የዘመናት ገድል ስንጠርቅ፣
ስንዘረዝር ስናወራ፣
ጣታችን መርፌ ሳይሰራ፣
ፈረንጅ በሰራው ስንኮራ፣
በዘመን አዙሪት ጥላ፣
ተመላልሰን ሁሌ ኋላ፣
የመገኘታችን መላ፣

ለምን ይሆን?

ከእም ነገደ ይሁዳ፣
የታሪክ የእምነት ጓዳ፣
አሪት ኣዲሱን ስንቀዳ፣
ከደብተራ አሪት እስከ መቅደስ፣
ጽላት ታቦቱ ሲነግስ፣
ቅኔ ማህሌቱ ሲፈስ፣

ኣውሮፓ ከእንቅልፏ ሳትነቃ፣
እኛ በጥበብ ቋንቋ፣
በያሬዳዊ ሙዚቃ፣
ገብተን ከመላእክት ጓዳ፣
ግእዝ እዝሉን ስንቀዳ፣

በቅኔ በመስዋእቱ፣
በከዋክብተ ሰማይ ጥናቱ፣
እንዳልተሰኘን ኣንቱ፣
ዛሬ ምንድን አሰረን፣
ከእድገት አምባ ተባረን፣
እንዲሁ በሜዳ የቀረን።

ለምን ይሆን?
ለምን ይሆን...
የእድገት ትልማችን ነጥፎ ፣
ተስፋችን ተንጠፍጥፎ ፣
የሆንነው የወሬ ከተፎ፣

ለምን?

ከመንደር እስከ ቀበሌ፣
ተቧድነን በዘር በጀሌ፣
ተስማምተን ላንደማመጥ፣
በነገር ስንቀጣቀጥ፣
በተንኮል ስንፈጣፈጥ፣
ስንቧደን በዘር ኣንጃ፣
ጸባችን ኣጥቶ ማብረጃ፣
ሁሌ ባለጠመንጃ፣
እንዱሁ በለው እንዳልን፣
ሰው ገለን እንደሸለልን፣
እስከመቼ እንዘልቃለን?

ኧረ ይብቃ ኅበዝ፣
ኣይነጥላችን ይገፈፍ፣
ይህ የታሪክ ጥቀርሻ ይርገፍ፣
ኣንለያይ እንተቃቀፍ።

ማለቱን ትተን ሁሌ የኔ፣
ተነስተን በስራ ወኔ፣
ቀለሃውን ወደ ጠመኔ፣
ወጥተን ከጥፋት ዋሻ፣
ጠመንጃውን ወደ ማረሻ፣
ለውጠን ሃገርን እናቅና፣
ታሪክ እንስራ እንደገና፣
ይህ ነው ሰው የሚያሰኘን፣
ከኣክሱም የሚያገናኘን፣
ከታሪክ የሚያጎዳኘን፣
ሰው ኣርጎ ቆሞ የሚዳኘን።

ኪያ.በ kiyakido@yahoo.com